# ከ"ድምፃችን ይሰማ' በስተጀርባ ያለ "አስፈሪ ጥላ"

(ከአብዱራህማን አህመዲን፤ የቀድሞ የፓርላማ አባል) (ahayder2000@gmail.com)

*(ይህ ጽሁፍ ዛሬ መስከረም 11 ቀን 2006 በወጣው ዕንቁ መጽሔት ላይ ታትሟል፡፡ መጽሔቱን የማያገኙ፣ በተለይም በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎች ሁሉ ቢያነቡት 'ይጠቅማል፤ ለመወያየም መነሻ ሊሆን ይችላል' በሚል ማኅፈስ በሚዲያ ሚድ ላይ እንዲታተም ተልኳል፡፡)*

አንዳንድ ጋዜጦች ላይ የማቀርባቸውን መጣጥፎች ያዩ አንዳንድ የማያውቁኝ ወገኖች፤ በሀገራችን ከፖለቲካው በላይ "እየጋለ" በመጣው በሙስሊሞች ጉዳይ ላይ ያለኝን አስተያየት እንድጽፍ ደጋግመው ይጠይቁኛል፡፡ በበኩሌ፣ በየጊዜው እርጥቡም ደረቁም እየተጨመረበት አልበርድ ባለ፣ ባልሰከነና የጠራ ባለቤት በሌለው ጉዳይ ላይ አስተያየት መስጠት አልፈለኩም ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፤ በተለያዩ አጋጣሚዎች የማያቸው፣ የምሰማቸውና የማነባቸው ነገሮች በዝምታዬ እንድገፋበት አላደረጉኝም፡፡ በአንድ በኩል፤ 'የሙስሊሞች ወኪል ነን' የሚሉ ወገኖች "ጥያቄ" ብለው የሚያነሷቸውን "ጥያቄዎች" የሙላው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ጥያቄዎች ናቸው ብዬ ለመውሰድ ይቸግረኛል፡፡ በሌላ በኩል፤ መንግስት "የሙስሊሞች ጥያቄ በሕገ-መንግስቱ ምላሽ አግኝቷል" ብሎ መደምደሙን ትክክል ነው ብዬ ለመቀበል ይቸግረኛል፡፡

እነዚህን ሃሳቦች በማውጠንጠን ላይ እንዳለሁ 'ድምፃችን ይሰማ' የሚባል (ሰው ይሁን ጅኒ ያለየለት) ነገር በፌስቡክ የሚያሰራጫቸውን የ"ተጠንቀቅ፣ አሳርፍ" ዓይነት "ወታደራዊ" ትእዛዞችን በተመለከተ በዕንቁ መጽሔት ቅጽ 6፣ ቁጥር 100፣ ጳጉሜ 2005 እትም ላይ ሁሴን ከድር የተባለ ጸሐፊ ያቀረበውን አነበብኩ፡፡

ወንድሜ ሁሴን ከድር ጋር በአካል እንተዋወቃለን፡፡ የጋራ የሆኑ ወንድሞችና ጓደኞችም አሉን፡፡ ሁሴን ለሀገሩና ለሃይማኖቱ ቀን ከሌት በቅንነት የሚተጋ ወንድም መሆኑን አስባለሁ፡፡ በእንቁ መጽሔት ላይ ያቀረባትም መጣጥፍ ይህንኑ ቅን አገልግሎቱን የምታመለክት ይመስለኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ሁሴን በመጣጥፉ ላይ ባነሳቸው አንዳንድ ሃሳቦች ላይ አልስማማም፡፡

ስለሆነም፤ በዚህ መጣጥፍ አንዱ የማነሳው ጉዳይ የሚልስማማበትን የሁሴንን ሃሳብ በተመለከተ ነው፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የማነሳው ጉዳይ የሙስሊሞችን ጥያቄ በተመለከተ ሲሆን፣ በሚጨረሻም "ድምፃችን ይሰማ' የሚባለውን 'የፌስቡክ መንፈስ' በተመለከተ ይሆናል፡፡ በዚሁ ቅደም ተከተል ሃሳቤን አቀርባለሁ፡፡

ጸሐፊ ሁሴን ለጽሁፉ የሰጠው ርዕስ "'ድምፃችን ይሰማ' ማን ነው?" የሚል መሆኑን ሳይ፤ ይህ ጅኒ ይሁን ሰው ያልታወቀ አካል ማን እንደሆነ ምላሽ የሚሰጥ መስሎኝ ነበር፡፡ እስከ ሜጨረሻው ሳነብ በጽሁፉ ርዕስነት ለቀረበው ጥያቄ የተሰጠው ሚልስ "'የድምፃችን ይሰማ' ማንነት እንቆቅልሽ እንደሆነ ዓመት ቆየ…" የሚል መሆኑን ተረዳሁ፡፡ ወንድሜ ሁሴን ምላሽ የሚይሰጥበትን ጥያቄ አንስቶ የጽሁፉ ርእስ ከሚያደርግ ይልቅ፤ ርዕሱን "ይፋ ያልሆነው 'ድምፃችን ይሰማ' ያከናወናቸው ተግባራት" ቢለው የተሻለ ይሆን ነበር የሚል እምነት አድሮብኛል፡፡

ጸሐፊው ከ"'ድምፃችን ይሰማ' እንቆቅልሽነት ጋር አስታኮ ያነሳው ሃሳብ ግን ፍፁም ስህተት ነው፡፡ እንዲህ ይነበባል፤ "ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማሪያም… 'ቅንጅት መንፈስ ነው' ብለው እንደነበር ይነገርላቸዋል…" ይላል፡፡ እኔም የቅንጅት ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባል ነበርኩ፡፡ ነገር ግን፣ እኔ እስከማውቀው ድረስ ፕሮፌሰር መስፍን እንዲህ ዓይነት ሃሳብ ተናግረው አያውቁም፡፡ ይህንን ሃሳብ

የተናገረችው ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ናት፡፡ ብርቱካን እንዳለቺው በርግጥም ቅንጅት ‘ማንፈስ’ እንጂ ‘ተቋም’ አልነበረም፡፡

ብርቱካን በዚያ ወቅት ‘ቅንጅት ማንፈስ ነው’ ያለቺው ግን የቅንጅትን ተቋም አለመሆን በአግባቡ ተረድታ አይመስለኝም፡፡ ምክንያቱም፤ ብርቱካን የቅንጅት አባል በሆነች ወር ባልሞላ ጊዜ ወስጥ የቅንጅት ተቀዳሚ ምክትል ፕሬዝዳንት ስለሆች ስለቅንጅት “ተቋምነትም” ይሁን “ማንፈስነት” የጠራ ግንዛቤ ነበራት ለማለት አያስደፍርም፡፡ እናም ንግግሯ ከደሙ-ነፍስ ንግግርነት የዘለለ፣ በእወቀት ላይ የተመሰረተ ሊሆን አይችልም፡፡

ሌላው በሁሴን ጽሁፍ ላይ ያየሁት ግድፈት፤ በጽሁፉ መግቢያ አካባቢ ላይ “‘ድምጻችን ይሰማ’ ይህ ጽሁፍ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ… ከ57 ሺህ በላይ ጎብኚ አለው…” ይለናል፡፡ (ይህ ጉብኝት በዕለት፣ በሳምንት፣ በወር ይሁን በዓመት አልተገለጸም) ወደ ጽሁፉ ማጠናቀቂያ አካባቢ ደግሞ እንዲህ ይላል፤ “‘ድምጻችን ይሰማ’ የተባለ የፌስቡክ ገጽ ሚሊዮኖችን በግራና በቀኝ አሰልፎ…” ይለናል፡፡

ምነው ወዳጄ ሁሴን! በሃምሳ ሰባት ሺህ እና በሚሊዮን መካከል እኮ ብዙ ብዙ ርቀት አለ፡፡ በኔ እምነት ቁምነገሩ የቁጥሩ ሚሊዮን ወይም ሺህ መሆን አደለም፡፡ አንድም ሰው ቢሆን ድምፁ ሊሰማ፤ ሃሳቡ ሊደመጥ ይገባል፡፡ እንዲያው ለነገሩ ከሃምሳ ሰባት ሺዎቹ የፌስቡክ ጎብኝዎች ወስጥ ምን ያህሉ ሙስሊሞች፣ አይሁዶች ወይም የሌላ እምነት ተከታዮች መሆናቸው ታውቆ ነው ወደ ሚሊዮን ስሌት የተገባው? ወይስ ድረ ገጹን የጎበኘ ሁሉ እንደ ደጋፊ ተወስዶ ይሆን? የተጣደፈ ድምዳሜ (Hasty Generalization) አይሆንም ወዳጄ?

“የሙስሊሞች ጥያቄ” ወደሚባሉት ጥያቄዎች እናምራ፡፡ በተለያዩ መገናኛ ብዙሃን ሲገለጹ እንደሰማሁትና ወንድሜ ሁሴንም በጽሁፉ መግቢያ አካባቢ ላይ እንደጠቀሰው “የሙስሊሞች ጥያቄ” ተብለው የሚነሱት ሦስት ናቸው፡፡ እነሱም - 1ኛ. የእስልምና ጉባዔ ጠቅላይ ምክር ቤት አመራር ምርጫን በተመለከተ፣ 2ኛ. የአህባሽ አስተምህሮን በግዳጅ ለማስፋፋት እየተሰጠ የነበረውን ስልጠና በተመለከተ፣ 3ኛ. የአወሊያ ትምህርት ቤትን አስተዳደር በተመለከተ፣ የሚሉ ናቸው፡፡

ቀደም ሲል ተቋቁሞ የነበረው የሙስሊሞች ጥያቄ መፍትሄ አፈላላጊ ኮሚቴም ሆነ ወንድም ሁሴን ከድርና ሌሎች ወገኖች እነዚህን ጥያቄዎች “የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄዎች ናቸው” ብለው ሲጠቅሱ እጅግ እጅግ ይገርመኛል፡፡ በግሌ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች እንደ ማህበረሰብ የሚያነሷቸው ወይም ሊያነሷቸው የሚገቡ ጥያቄዎች እንዳሏቸው አምናለሁ፡፡ እነዚህ ከላይ የጠቀስኳቸው ሦስት ጥያቄዎች ግን የመላው ኢትዮጵያዊ ሙስሊም ጥያቄ ተደርገው ሊወሰዱ ይችላሉ የሚል እምነትም ግምትም የለኝም፡፡ ይህንን ሃሳቤን እንደሚከተለው አብራራለሁ፡፡

ከሚጨረሻወና ቀለል ካለው ጥያቄ እንነሳ፡፡ የአወሊያ ትምህርት ቤት አስተዳደር ጉዳይ እንደ ጥያቄ መነሳቱ ተገቢ መሆኑን አስባለሁ፡፡ ነገር ግን ይህ ጥያቄ የአዲስ አበባ (ያውም መርካቶ አካባቢ ያሉ፣ እነሱም ቢሆኑ ልጆቻቸውን በዚያ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ) ሙስሊሞች ጥያቄ እንጂ የመላው ኢትዮጵያዊ ሙስሊሞች ጥያቄ ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም ባይ ነኝ፡፡ የአንድ አካባቢ ማህበረሰብ ጥያቄዎች በየትኛውም መመዘኛ በሚሊዮን የሚቆጠሩ የማህበረሰቡ አባላት ጥያቄዎች ተደርገው ሊወሰዱ አይችሉም፡፡ ለምሳሌ፡- አርሲ ወስጥ ወይም በሌላ አንዲት የገጠር መንደር የሚኖሩ ሙስሊሞች ያቋቋሙት የአወሊያ ዓይነት ትምህርት ቤት (መድረሳ) ቢሆን ኖሮ ያን ያህል ተጋኖና “የሙስሊሞች ጥያቄ” ተደርጎ የሚቀርብበት ሁኔታ ሊኖር ይችል ነበር?

እውነቱን እንነጋገር ከተባለ የአወሊያ ጉዳይ “የሙስሊሞች ጥያቄ” ተደርጎ የቀረበው ችግሩ አዲስ አበባ ላይ የተፈጸመ በመሆኑ እንጂ ጥያቄው መላውን ኢትዮጵያዊ ሙስሊም የሚመለከት በመሆኑ አይመስለኝም፡፡ ይህ ማለት ግን መላውን ሙስሊም የማይመለከቱ መለስተኛ (አካባቢያዊ) ጥያቄዎች አይነሱ፣ ምላሽም አይሰጣቸው ማለት አደለም፡፡ ሙስሊሞች በመቶዎች የሚቆጠሩ ጥያቄዎች ቢኖሯቸው፤ እነዚያ ጥያቄዎች ሊመለሱ የሚችሉት ግን እንደ ክብደታቸውና እንደ አስቸኳይነታቸው እየታዩ በቅደም ተከተል መሆኑን ማዝንጋት ያለብን አይመስለኝም፡፡

ሁለተኛውን ጥያቄ እንይ፡፡ ‘የአህባሽ አስተምህሮ (ልክ እንደ ወሃቢያ አስተምህሮ) ለኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚበጅ በመሆኑ ሊስፋፋ አይገባውም’ የሚል ሃሳብን እንደ ጥያቄ ማንሳት ችግር ያለው አይመስለኝም፡፡ ሀጢያትም ወንጀልም አድርጎ መውሰድም የሚቻል አይመስኝም፡፡ ሀጢያትም ወንጀልም ሊሆን የሚችለው ይህንን አስተምህሮ እንከተላለን የሚሉ ወገኖች አስተምህሮቱን እንዳያስተምሩ ማከልከል ይመስለኛል፡፡

የሆነ ሆኖ የአህባሽ አስተምህሮ ተሰጠ የተባለው በሁለት ከተሞች፣ ያውም በአነስተኛ አዳራሽ ውስጥ፣ ለዚያውም በመቶዎች ለሚቆጠሩ ሰዎች መሆኑን ነው የሰማሁት፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ‘የአህባሽ አስተምህሮ ጠንቀኛ ነው፤ ሙስሊሙ ህብረተሰብም አይቀበለውም’ የምንል ከሆነ፤ የፈለገውን ያህል ‘መንግስት ይደግፈዋል’ ቢባል እንኳ (ሙስሊሙ ህብረተሰብ ወዶና ፈቅዶ እስካልተቀበለው ድረስ) የሚያመጣው ችግር አይታየኝም፡፡ ወዶና ፈቅዶ ከተቀበለው ደግሞ “ከባለቤቱ ያወቀ…” ብለን ከማለፍ ዉጪ ምን ማድረግ እንችላለን? ምክንያቱም ቅዱስ ቁርዓን “በሃይማኖት ማስገደድ የለም” በማለት የደነገገውን በማዝንጋት ፀጉራችንን መንጨት ያለብን አይመስለኝም፡፡ እናም ይህንን ጥያቄ እንደ ጥያቄ የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን ይወክላል ብሎ፣ የቅድሚያ ቅድሚያ ሰጥቶ በዚህ ወቅት ማንሳቱ ፋይዳም ትርጉምም ያለው ሆኖ አይታየኝም፡፡ በነገራችን ላይ የአህባሽ አስተምህሮ ማስፋፋት ከሁሉም በላይ የሚጎዳው መንግስትን እንጂ እስልምናን እንዳልሆነ በድፍረት መናገር ይቻላል፡፡ (በዚህ ጉዳይ ላይ ወደኋላ ላይ እመለስበታለሁ)

ወደ ሌላኛው ጥያቄ እናምራ፡፡ የምርጫ ዘመኑን ያሳለፈው መጅሊስን በተመለከተ የተነሳው ጥያቄ በርግጥም መላውን ሙስሊም ማህበረሰብ የሚመለከት ጥያቄ አድርጎ መውሰድ የሚቻል ይመስለኛል፡፡ ይህንን ጥያቄ መንግስትም ቢሆን ተቀብሎት “በሚፈልገው መልኩ” ምላሽ እንዲያገኝ አድርጓል፡፡ እኔ እንደሚስታወሰው ዱሮም የመጅሊስ አመራር ለዘመናት ሲመረጥ የነበረው “መንግስት በሚፈልገው መልኩ አልነበረም” ብሎ ለመከራከር የሚቻል አይመስለኝም፡፡ እናም አሁን አዲስ ነገር እንደተፈጠረ አካኪ ዘራፍ ማለቱ ተገቢ ነው ብዬ ለመውሰድ ይቸግረኛል – ሌላ ፍላጎት ከሌለንና መንግስት ጋር መጫቃጨቅ ካላማረን በስተቀር!

እዚህ ላይ “እስከ ዛሬ ጥያቄውን ስላላነሳን ዛሬ ማንሳት የለብንም ወይ?” የሚል መከራከሪያ ማንሳት ይቻላል፡፡ በዚህ ረገድ እኔ ያለኝ እይታ ለየት ያለ ነው፡፡ የተለያዩ ምክንያቶችንና ቅድመ ሁኔታዎችን እየደረደርን የመጅሊስ ምርጫ እንዳይካሄድ ከማድረግ ይልቅ፤ በእጩነት፣ በመራጭነትና በአስመራጭነት መሳተፍ አይሻልም ወይ የሚል ጥያቄ አለኝ እኔ፡፡ በኔ እምነት በአንድ ምርጫ ሁሉም ችግሮች ይወገዳሉ ብሎ ማሰብ የዋህነት ነው፡፡ ስለሆነም፤ ዘመናቸውን ያጠናቀቁትን አሰናብቶ ስለቀጣዩ ማሰብ ነው የሚሻል፡፡

ምርጫው በመስጊድ ወይም በቀበሌ በመካሄዱ የሚፈረውን አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ሁኔታ ማወቅ የሚቻለውም መጀመሪያ ምርጫው በአንዱ ስፍራ ሲካሄድ ነውና በዚህም ረገድ ተቀስቅሶ የነበረው ወዝግብ ትክክል አይመስለኝም፡፡ ልክ እንደ ተቃዋሚ ፓርቲ ሁልጊዜ መንግስት የሚለውን ሁሉ በጥርጣሬ መመልከትም ጠቃሚ መንገድ አይመስለኝም፡፡ እኛ ሙስሊሞች “አላህ የትም ቦታ አለ” ብለን የምናምን እስከሆነ ድረስ ምርጫው በቀበሌ ተካሄደ በመስጊድ ሁሉም ነገር በአላህ ፈቃድ መሆኑ እንደሁ አይቀሬ ነው፡፡ እናም ፀሎታችንን እያደረስን ስራችንን መስራት ነው ትክክለኛው መንገድ፡፡

ስለሆነም፤ ወንድሜ ሁሴን ከድርም ሆነ አንዳንድ ወገኖች “የሙስሊሞች ጥያቄ” እያሉ የሚያነሷቸው “ጥያቄዎች” ከላይ ለማሳየት በሞከርኩት መልኩ ቢታዩ መልካም ነው፡፡ ከጥያቄዎቹ ፋይዳ አኳያም ያን ያህል ከመንግስት ጋር መፋጠጥና ሰንደቅ ዓላማን እስከ መቅደድ መሄድ አስፈላጊ መስሎ አይታየኝም፡፡

ይህ እንዳለ ሆኖ፣ በኔ እምነት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄዎች እንዳሏቸው አስባለሁ፡፡ በመንግስት በኩል “የሙስሊሞች ጥያቄዎች በሕገ-መንግስቱ አማካይነት ምላሽ አግኝተዋል” የሚለውን ሃሳብ በበኩሌ አልቀበልም፡፡ የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጥያቄዎች በሕገ-መንግስቱ “እውቅና ተሰጥቷቸዋል” የሚለውን እቀበላለሁ፡፡ እነዚህ ሕገ መንግስታዊ እውቅና ያገኙ ጥያቄዎች ግን “የተግባር ምላሽ” አላገኙም፡፡

እዚህ ላይ ለመሆኑ የተግባር ምላሽ ያላገኙት የሙስሊሞች ጥያቄዎች የትኞቹ ናቸው? የሚል ጥያቄ ቢነሳ ተገቢ ነው፡፡ በኔ እምነት የኢትዮጵያ ሙስሊሞች የሚያነሷቸው ወይም ሊያነሷቸው የሚገቡት ተግባራዊ ምላሽን የሚሹ ጥያቄዎች በአጭሩ በሁለት ቃላት፤ “የተጠቃሚነት” እና “የፍትሃዊነት/እኩልነት” ጥያቄዎች ተብለው ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ቃላት በቁጥር ‘ሁለት’ ቢሆኑም በውጣቸው በርካታ ጉዳዮችን

አምቀው እንደያዙ የሚያውቅ ያውቀዋል፣ የሚባባው ይገባዋል፡፡ እነዚህ ጥያቄዎችም ቢሆኑ የሚሟሉት ግን መንግስት ጋር በመፋጠጥ፣ ትኩር ጥምድ ውስጥ በመግባት፣ ለልማት የሚውልን ጊዜና ጉልበት፣ ሀብትና ንብረት በማባከን ሊሆን አይገባወም፡፡

ያለነው 21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ ነው፡፡ ፍልስጤማውያን እና እስራኤላውያን እንኳ ወደ ድርድር ፖለቲካ እየተሟሉ ነው፡፡ እኛም በምክክርና በውይይት የማንፈታው ጉዳይ ሊኖረን አይችልም፡፡ ለዚህ ደግሞ እስልምና በርካታ ተሞክሮዎች ስላሉት እነዚያን መንገዶች መጠርጠር ነው፡፡ እነ አባባ አሜዴ ለማ (አላህ ይማራቸው) በሕይወት ባይኖሩም ኢትዮጵያዊ የሽምግልና ባህላችን ትልቁ የችግር (የግጭት) መፍቻ መዛሪያችን ነው፡፡ ከእኔ ጀምሮ የመንግስት "ጓዳዎችን" እና ባለስልጣናትን በቅርበትም በርቀትም የምናውቅ ሰዎች ባለንበት ሀገር፤ ማከብ፣ ማጋገርና መደማመጥ አቅቶን ጊዜ ማባከን፣ ሀብትና ንብረት መውደም፣ ሰው መታሰር ነበረበት?

በመጨረሻ፤ ጸሀፊ ሁሴን ከድር በርዕስነት ያነሳውን ጥያቄ በተመለከተ ያለኝን አስተያየት ላንሳ፡፡ ወንድሜ ሁሴን በጽሁፉ ላይ እንዳመለከተው "ድምፃችን ይሰማ" በዓይን የሚታይ ወይም በእጅ የሚዳሰስ፣ ጅን ይሁን ሰው፣ እስላም ይሁን አይሁድ፣ ግለሰብ ይሁን ቡድን፣... ምንነቱ ያልለየ ነገር ነው፡፡ ይህም በመሆኑ ከዚህ አካል በስተጀርባ ያለው "ጥላ" በግሌ እጅግ ያስፈራኛል፡፡ ያሳስበኛልም፡፡ የዚህን "አካል" የፌስቡክ ገጽ ለጥቂት ቀናት አይቻለሁ፡፡ ያየሁትና ያነበብኩት ነገር ነው ይበልጥ ያሳሰበኝ፡፡

በኢትዮጵያ የተቃውሞ ፖለቲካ ውስጥ ለአስራ ሁለት ዓመታት ገደማ በከፍተኛ አመራርነት ጭምር አሳልፌአለሁ፡፡ ዋና ዋና የሚባሉትን የፖለቲካ ሰዎች አውቃቸዋለሁ፣ አብሬአቸውም ሰርቻለሁ፡፡ ድክመትና ጥንካሬአቸውንም አስተውያለሁ፡፡ "ድምፃችን ይሰማ" እንደሚባለው አካል ግን ጥንቃቄ በተሞላበት አኳኋን፣ ጊዜና ሁኔታን አገናዝበው መንግስትን ለማስጨነቅና ለመወጠር ሲሰሩ አይቼ አላወቅም፡፡ ለዚህም ነው ከ"ድምፃችን ይሰማ" በስተጀርባ ጥሩ የፖለቲካ ተንታኝ፣ ግንዘቤና እውቀት ያለው "አካል" አለ የሚል እምነት ያደረብኝ፡፡

የሚያስፈራኝ የ"ድምፃችን ይሰማ" የሚያቀርበው ጽሁፍ መልእክት አደለም፡፡ የሚያስራኝ ይህንን አካል የሚመሩት ሰው/ሰዎች አስተሳሰብና ፍልስፍና፣ ይዘውት የተነሱት ራዕይ፣ አይዲዮሎጂ... በግልጽ አለመታወቁ ነው፡፡ ያ ማንነቱ ያልታወቀ የፌስቡክ አካል "መጥፎን ይከለክላል፣ ፍቅርን ይሰብካል፣ ፀብን ይጠላል፣..." የሚል መልእክት የሚያስተላልፍ መሆኑን ሁሴን ከድር በጽሁፉ ላይ አስነብቦናል፡፡ ወዳጄ ሁሴን ያገሬ ሰው ምን እንደሚል ታውቃለህ? አዎ! ያገሬ ሰው "ሰይጣንም ለብልሃቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል" ይላል፡፡ የስጋቴ ምንጭ ይኸው ነው!!! ጩልማን ተገን አድርጎ ማቅለቅ ቀላል ነው፡፡

ጽሁፌን ከመቋጨቴ በፊት አንዳንድ የሚጠቃለያ ሃሳቦችን ላቅርብ፡፡ የመቋጫ ሃሳቤ በዋናነት በመንግስት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ መንግስት በአዲስ ዓመት በአዲስ መንፈስ ሦስት ነገሮችን ደግሞ ደጋግሞ ቢመረምራቸው መልካም ነው እላለሁ፡፡ ይኸውም - አንደኛ "የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ያልተሟሉ ጥያቄ የለም" የሚለውን በተመለከተ ነው፡፡ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ዛሬም የተግባር ምላሽ ያላገኙ "የተጠቃሚነት" እና "የፍትሃዊነት/እኩልነት" ጥያቄዎች አሏቸው፡፡ እናም መንግስት በዚህ ረገድ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ለመሙላት ትኩረት ሰጥቶ ማስራት ይጠበቅበታል፡፡

ሁለተኛ፤ በመንግስት በኩል መታየት ያለበት የእስልምና አስተምህሮቶችን በተመለከተ ነው፡፡ አንዳንድ የመንግስት ባለስልጣናት የወሐቢይ አስተምህሮትን ከአክራሪነትና ከአሸባሪነት ተግባር ጋር በማያያዝ ሲገልጹ ሰምቻለሁ፡፡ በዚህ ላይ ብዙም ልዩነት የለኝም፡፡ ነገር ግን የአህባሽ አስተምህሮትም ቢሆን ከወሃቢይ አስተምህሮት እኩል ሊወገዝ የሚባባው ጽንፈኛ የጥፋት መንገድ መሆኑን ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ የሃይማኖት ስብጥር መናኸሪያ ለሆነቺው ኢትዮጵያ እንደማይበጃትም ይናገራሉ፡፡

ወሐቢያን መንግስትም ጣልቃ ሳይገባ ራሱ ሕዝቡ ሲከላከለው የኖረው ነው፡፡ የዛሬ ሃያ ዓመት ገደማ ወሐቢዎች ጀበና ማስበር ሲጀምሩ ሕዝቡ ራሱ ነው ያከሰማቸው፡፡ አህባሽ ከወሃቢያ የባሰ ለዘመናት የገነባናቸውን ኢትዮጵያዊ እሴቶቻችንን የሚያወድም የጥፋት ኃይል መሆኑን ሕዝቡ ስለሚያውቅ አይቀበለውም፡፡ ነገር ግን አንዳንድ የህብረተሰብ ክፍሎች ጋር ያለው ስጋት "አህባሽ የመንግስት ይሁንታ አለው" የሚለው ነው፡፡ ሕዝቡን የሚያስፈራው ይሄ ነው፡፡

በርካታ ሙስሊም ምሁራን እንደሚሉት ከሆነ፤ በሰለፊ ሙቀፍ ወስጥ ካሉት አስተምህሮቶች ‘ወሐቢያ’፤ በሱፊ ሙቀፍ ወስጥ ካሉት አስተምህሮቶች ደግሞ ‘አህባሽ’ ጽንፈኛ እንደሆኑ ይናገራሉ፡፡ “አህባሽ ለኢትዮጵያ የማይጠቅም የተሳሳተ ሞዴል (Wrong Model) ነው፡፡ መንግስት ይህንን አልተረዳወም” ነው የሚሉት ምሁራኑ፡፡ ስለሆነም መንግስት ሁለቱን ጽንፈኛ አስተምህሮዎች ህብረተሰቡ ተገንዝቦ ራሱን እንዲጠብቅ የመደገፍ እንጂ ለአንዱ ይሁንታ ሰጥቶ አንዱን በማውገዝ የሚፈለገወን ወጤት ሊያመጣ አይችልም፡፡

ከዚህ በተጨማሪ መንግስት ማድረግ ያለበት ሦስተኛው ነገር ከሽብር ተግባር ጋር በተያያዘ ተጠርጥረው የተያዙትን በተመለከተ ነው፡፡ በዚህ ረገድ መንግስት ሆደ ሰፊነቱንና ታላቅነቱን ቢያሳይ መልካም ነው፡፡ ከታሰሩት ወስጥ በቅርበትም በርቀትም የማውቃቸው ወንድሞች አሉ፡፡ መደማመጥ አልተቻለም እንጂ ይህ ሁሉ እንዳይከሰት ምክርም፣ ዝክርም ሰጥቼ ነበር፡፡ በማወቅም ባለማወቅም ስህተት የፈጸሙ እንደሚኖሩ አስባለሁ፡፡ ያጠፉ መቀጣት እንዳለበትም አምናለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ብዙዎቹ ልጆች ናቸው፡፡ ቁንጥጫ ይበቃቸዋል፡፡ አስተምሮ፣ መክሮና ዘክሮ መልቀቅም እኮ ቅጣት ነው፡፡

መንግስት ሁልጊዜ የሕግ ሂደቱን ጨርሶ ይቅርታ (pardon) ማድረግን ብቻ ማሰብ የለበትም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ምህረት (mercy) ማድረግም አስፈላጊ መሆኑን ቢያየው መልካም ነው፡፡ ለእነዚህ “ልጆች” ምህረት ቢያደርግ ዓርብ ዓርብ የሚደረገው “የመስጊድ ጩኸትና ዱብ እንቅ” በአንድ ጊዜ ቀጥ ብሎ እንደሚቆም አስባለሁ፡፡ እናም ከአዲሱ ዓመት ጋር አያይዞ በምህረት ቢፈታቸው አይሻልም?

አዲሱን ዓመት የምህረት ዘመን ያድርግልን!!!